የግዕዝ ጉባኤ ቃና

- መደብ መጀመሪያ ተነሽ ተጣይ ከ፪ እስከ ፬ ሰያፍ ከ፫ እስከ፭ ወዳቂ ከ፩ እስከ ፫::
  - ❖ የተነሽና የሰያፍ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ ፪፪ ሰያፍ ፫፫
- የተጣይ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ ፪ም ፫ም ሰያፍ ፫ም ፬ም
- የወዳቂ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ ፫፫ ሰያፍ ፬፬
  - ➢ ለወዳቂ መደብነት እንጅ ተቀባይነት አልቦ
- ○ የቤት መምቻው መደብ መጀመሪያ ተነሽ ከ፭ እስከ፯ ሰያፍ ከ፮ እስከ፰ ተጣይ ከ፮ እስከ፯ ወዳቂ ከ፭ እስከ፮
  - ❖ የ፭ቱ ተነሽ የ፮ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ ወዳቂ እንበለ ሰያፍ ፫፫
  - ❖ የ፮ቱ የ፯ቱ ተነሽ የ፯ቱ የ፰ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ ወዳቂ እንበለ ሰያፍ ፪፪
  - ❖ የ፮ቱ የ፯ቱ ተጣይ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ ወዳቂ እንበለ ሰያፍ ፪ም ፫ም
  - ❖ የ፭ቱ የ፮ቱ ወዳቂ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ ወዳቂ ያለሰያፍ ፫፫
- **የ፪ኛው ቤት**
- ❖ መደብ መጀመሪያ በዕዝልም በግዕዝም ኾኖ ተቀባዩ እስከ ቤት መምቻው አይለወጥም፡፡

የዕዝል ጉባኤ ቃና

- መደብ መጀመሪያ ተነሽ ተጣይ ከ፪ እስከ፯ ፭ን አይነካም ሰያፍ ከ፫ እስከ፰ ፮ን አይነካም ወዳቂ ከ፩ እስከ፮ ፬ን አይነካም
  - ❖ ተቀባዩ እንደ ግዕዙ ጉባኤ ቃና ነው
  - ○ የሐረጉ ልክ ተነሽ ተጣይ ሰያፍ ከ፬ እስከ፭ ወዳቂ ከ፫ እስከ፭
- የ፪ኛው ቤት ግን ሐረጉ ወዳቂ ብቻ ፫፫፡፡

የዘአምላኪየ

- መደብ መጀመሪያ እንደ ግዕዝም እንደ ዕዝልም ጉባኤ ቃና ነው
  - ❖ ተቀባዩም ከማሁ
- ○ ቤት መምቻውም መደቡም እስከ ተቀባዩ ከማሁ
- የማንደርደሪያው መደብ መጀመሪያ ተነሽ ተጣይ ከ፪ እስከ፬ ሰያፍ ከ፫ እስከ፭ ወዳቂ አልቦ
  - ❖ ማረፊያው በተናባቢ እንበለ ሰያፍ ፮፮

- የቤት መምቻው መደብ መጀመሪያ ተነሽ ከ፫ እስከ፬ ሰያፍ ከ፬ እስከ፭ ተጣይ ፴፬ ወዳቂ ፫፫
  - የ፫ቱ ተነሽ የ፬ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ ወዳቂ እንበለ ሰያፍ ፫፫
  - የ፬ቱ ተነሽ የ፭ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ ፫ቱ ንባባት እንበለ ሰያፍ ፪፪
  - የ፬ቱ ተጣይ መደብ ተቀባይ ፫ቱ ንባባት እንበለ ሰያፍ ፪ም ፫ም
  - የ፫ቱ ወዳቂ መደብ ተቀባይ ፫ቱ ንባባት እንበለ ሰያፍ ፫፫።

➢ የአጭሩ ማንደርደሪያ

- መደብ መጀመሪያ ተነሽ ተጣይ ከ፪ እስከ፬ ሰያፍ ከ፫ እስከ፭ ወዳቂ ከ፭ እስከ፫
  - የ፪ቱ የ፫ቱ ተነሽ የ፫ የ፬ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ ወዳቂ ብቻ ፫፫
  - የ፬ቱ ተነሽ የ፭ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ ወዳቂ ብቻ ፪፪
  - የ፪ቱ የ፫ቱ የ፬ቱ ተጣይ መደብ ተቀባይ ወዳቂ ብቻ ፪ም ፫ም
  - የ፭ዱ የ፪ቱ የ፫ቱ ወዳቂ መደብ ተቀባይ ወዳቂ ብቻ ፫፫
- ቤት መምቻው ከማሁ

➢ እንደገና

- በቤት መምቻ ሲኾን ተነሽ ከ፫ እስከ፬ ሰያፍ ከ፬ እስከ፭ ተጣይ ፴፬ ወዳቂ ፫፫
  - የ፫ቱ ተነሽ የ፬ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ ወዳቂ ብቻ ፫፫
  - የ፬ቱ ተነሽ የ፭ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ ወዳቂ ብቻ ፪፪
  - የ፬ቱ ተጣይ መደብ ተቀባይ ወዳቂ ብቻ ፪ም ፫ም
  - የ፫ቱ ወዳቂ መደብ ተቀባይ ወዳቂ ብቻ ፫፫
- ቤት መምቻውም ከማሁ

➢ **ያለማስነሻ** ማንደርደሪያ ይኾናል

- ፫ኛው ቤት በዕዝልም በግዕዝም እንደ ጉባኤ ቃና ነው ሐረጉ ወዳቂ በተለየ ፫፫ ብቻ
- ቤት መምቻው ከማሁ

የሚበዝኑ

- መደብ መጀመሪያ እስከ ቤት መምቻው በዕዝልም በግዕዝም እንደ ጉባኤ ቃና
- ቤት መምቻው በልውጥ ሲኾን መደቡ ዕዝል ጉባኤ ቃና ነው

- ❖ ተቀባዩ የተነሸና የሰያፍ ፬ቱ ንባባት ሁሉ ፬፬
- ❖ የተጣይ ፬ቱ ንባባት ፬ም ፭ም
- ❖ የወዳቂ ፬ቱ ንባባት ፭፭

- የ፪ኛው ቤት ልክ በዕዝልም በግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው ቤት መምቻውም ከማሁ
- ፫ኛው ቤት በዕዝልም በግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው ቤት መምቻውም ከማሁ።።

የዋዜማ

- መደብ በዕዝልም በግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው
  - ➢ ለወዳቂ ተቀባይነት እንጅ መደብነት አልቦ
  - ❖ ተቀባዩ ፬ቱ ንባባት ሁሉ ፬ም ፭ም
- ○ ቀጥሎ ያለው በዕዝልም በግዕዝም እንደ ጉባኤ ቃና ነው
- ○ ቤት መምቻውም ከማሁ
- ማንደርደሪያውም ከዘአምላኪየ ላይ እንደተነገረው ነው
- ፫ኛው ቤት እስከ ቤት መምቻው በዕዝልም በግዕዝም እንደ ጉባኤ ቃና ነው
- የመጽፊያው መደብ እስከ ተቀባዩ በዕዝልም በግዕዝም እንደ ጉባኤ ቃና ነው
- ○ ቤት መምቻው ተነሽ ተጣይ በተናባቢ ፮፮ ወዳቂ ፬ም ፭ም ሰያፍ አልቦ
- ➢ የመጽፊያው ቤት መምቻ መደብ በግዕዝ ጉባኤ ቃና መደብ ሲሆን
  - ❖ የተነሸና የሰያፍ መደብ ተቀባይ ያለ ሰያፍ ያለ ወዳቂ ተነሽ ተጣይ ፪፪
  - ❖ የተጣይ መደብ ተቀባይ እንበለ ሰያፍ እና እንበለ ወዳቂ ተነሽ ተጣይ ፪ም ፫ም
  - ❖ የወዳቂ መደብ ተቀባይ ያለ ሰያፍና ያለወዳቂ ተነሽ ተጣይ ፫፫
- የ፭ኛው ቤት ማንሻው እንበለ ሰያፍ ፫ቱ ንባባት ፬፬
- ○ የቤት መምቻው መደቡ ከነተቀባዩ የማንደርደሪያው ቤት መምቻ ነው።።

አጭር ዋዜማ

- ማንደርደሪያውና ከማንደርደሪያው ቀጥሎ ያለው ነው።።

መስኮት ዋዜማ

- የዐቢይ ዋዜማ መጀመሪያው ቤትና መጽፊያው መጨረሻው ቤት በሙሉ ነው።።

የሥላሴ

- መደብ መጀመሪያ እንበለ ወዳቂ ግዕዝ ጉባኤ ቃና ነው
  - በዕዝል አይነሳም
    - ተቀባዩ ፱ቱ ንባባት ፱ም ፭ም በተናባቢ ግን ፱ቱ ንባባት ፮፮
  - ኃይለ ቃሉ ተነሽ ተጣይ ከ፮ እስከ፯ ሰያፍ ከ፯ እስከ፰ ወዳቂ ከ፭ እስከ፮
    - የተነሽና የሰያፍ መደብ ተቀባይ ፱ቱ ንባባት ፱፱
    - የተጣይ መደብ ተቀባይ ፱ቱ ንባባት ፱ም ፭ም
    - የወዳቂ መደብ ተቀባይ ፱ቱ ንባባት ፭፭
  - ከዚኽ ቀጥሎ መደቡ ከነተቀባዩ በዕዝልም በግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው
  - ሐረጉም ወዳቂ ብቻ ፫፫ ነው
  - የቤት መምቻውም መደቡ ከነተቀባዩ እንደ ጉባኤ ቃና ነው
- ማንደርደሪያውም ከማሁ
- የ፫ኛው ቤት ሐረግ ወዳቂ ፫፫ ኾኖ በዕዝልም በግዕዝም እስከ ቤት መምቻው እንደ ጉባኤ ቃና ነው
- የ፱ኛው ቤት ልክ እንደ መጀመሪያው ኃይለ ቃል ነው
  - በግዕዝ ጉባኤ ቃና ሲሆን ማረፊያው ፱ቱ ንባባት ፭፭
  - ፱ቱ ኃይለ ቃሎች በዜማ ልክ ፭ ናቸው
- የ፭ኛው ቤት ልክ እንደ ዋዜማ መጽፊያ ነው
  - ሰያፍም በተናባቢ ፮፮ ይኾናል
- ፮ኛው ቤት እንደዋዜማው መጨረሻ ቤት ነው።።

የዘይእዜ

- መደብ መጀመሪያ በግዕዝ በዕዝልም ጉባኤ ቃና ነው
  - ማረፊያው ፱ቱ ንባባት ፭፭
  - በልውጥ ሚበዝኑም ይጀምራል
  - ቀጥሎ መደቡ ከነተቀባዩ እስከ ቤት መምቻው ያለሐረግ በዕዝልም በግዕዝም እንደ ጉባኤ ቃና ነው
- የኀይለ ቃሉ መደቡ ከነተቀባዩ ልውጥ ሚበዝኑ ነው

- እንደ መጀመሪያውም ማድረግ ይቻላል
  - ማንደርደሪያው የተለመደው ነው
- የ፫ኛው ቤት መደቡ ከነተቀባዩ በዕዝልም በግዕዝም እንደ ጉባኤ ቃና ነው
  - ቤት መምቻው ልውጥ ሚበዝኑ ነው
- የ፬ኛው ቤት መደቡ ከነተቀባዩ በዕዝልም በግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው
  - ማረፊያው ፬ቱ ንባባት ፮፮
- የ፭ኛው ቤት መደቡ ከነተቀባዩ እስከ መጨረሻው በዕዝልም በግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው::

የሣህልክ ፣

- መደቡ እስከ መጨረሻው ፫ት ቤት ኾኖ አይለወጥም እንደ ዘይእዜ ነው
  - ፪ት ቤትም ይኾናል፡፡

የመወድስ

- መደብ መጀመሪያው ከነተቀባዩ በዕዝልም በግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው
  - ማረፊያው ፬ቱ ንባባት ፮፮
  - ቀጥሎ ያለው መደቡ ከነተቀባዩ በዕዝልም በግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው
  - ቤት መምቻውም ከማሁ
    - በልውጥ ሚበዝኑም ይኾናል
- የ፪ኛው ቤት መደቡ ከነተቀባዩ እስከ ቤት መምቻው በዕዝልም በግዕዝም እንደ ጉባኤ ቃና ነው
  - ቤት መምቻው በተለየ በተናባቢ ፬ቱ ንባባት ከ፬ እስከ፮ ይኾናል
- ኀይለ ቃሉ እንደ ዘይእዜ ነው
  - ማንደርደሪያው ከማሁ
- ፬ኛው ኀይለ ቃል መደቡ ከነተቀባዩ ልውጥ ሚበዝኑ ነው
    - ከዚኽ ላይ ተቀባዩና ቤት መምቻው ፭ ስለኾነ ስለኵልክሙ ይቆጠራል
  - ቀጥሎ ያለው መደቡ ከነተቀባዩ በዕዝልም በግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው
  - ቤት መምቻውም ከማሁ በልውጥ ሚበዝኑም ይኾናል
- ለዓለሙ በሂ በኒ በሰ ሲከፈል ምንጊዜም ወዳቂ ስለኾነ መደቡ ወዳቂ ብቻ ከ፫ እስከ፮
- ተቀባዩ ፬ቱ ንባባት ፬ም ፭ም

- የቤት መምቻ መደቡ ከነተቀባዩ እንደጉባኤ ቃና ነው
  - እንደገና ለዓለሙ ሳይከፈል በልውጥ ይነሳል
- ማረፊያውም ከ፬ እስከ፯ ኾኖ ፬ቱ ንባባት ቤት መምቻ ይኾናል
  - በልውጥ ተነስቶ በጉባኤ ቃናም ቤት ይመታል
- የ፯ኛው ቤት መደቡ ከነተቀባዩ ልውጥ ሚበዝኑ ነው ቤት መምቻውም ከማሁ
- የ፯ኛው ቤት መደቡ ከነተቀባዩ በዕዝልም በግዕዝም እስከ ቤት መምቻው ጉባኤ ቃና ነው
- ፰ኛው ቤት እንደ ፯ኛው ቤት ነው

ከልክሙ ሲኾን

- ከዚህ ላይ ያለሐረግ በዕዝልም በግዕዝም ፩ ቤት ጉባኤ ቃና መጨመር ነው::

አጭር መወድስ

- በግዕዝ ጉባኤ ቃና ጀምሮ በጉባኤ ቃና ቤት መቶ በማንደርደሪያ መጨረስ ነው::

የግዕዝ ክብር ይእቲ

- መደብ መጀመሪያ በዕዝል በግዕዝ ጀምሮ እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው
  - የቤት መምቻው መደብ እስከ ተቀባዩ ልውጥ ሚበዝኑ ነው
- ፪ኛው ቤትና ፫ኛው ቤት በዕዝልም በግዕዝም ፍጹም ጉባኤ ቃና ነው
- ፬ኛው ቤት እንደ መጀመሪያው ነው::

የግዕዝ ዕጣነ ሞገር

- መደብ መጀመሪያ በዕዝል በግዕዝ ጉባኤ ቃና ነው ተቀባዩም ከማሁ
  - ቀጥሎ ያለው እስከ ተቀባዩ ከማሁ
  - ሐረጉ ተነሽ ተጣይ ሰያፍ ከ፬ እስከ፭ ወዳቂ ፫ እስከ፭
  - ቤት መምቻው ልውጥ ሚበዝኑ ነው
- ፪ኛው ቤት እስከ ቤት መምቻው ያለሐረግ በዕዝልም በግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው
- ፫ኛው ቤትም ከማሁ ማንደርደሪያውም ከማሁ

- ፭ኛው ቤት እስከ ተቀባዩ በዕዝልም በግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው
  - ሐረጉ እንደመጀመሪያው ነው
  - ቤት መምቻው ልውጥ ሚበዝኑ ነው
- ፮ኛው ቤት ሐረጉ ከማሁ ኾኖ በዕዝልም በግዕዝም እስከ ቤት መምቻው ጉባኤ ቃና ነው
- ፯ኛው ቤት መደቡ እስከ ተቀባዩ እስከ ማረፊያው ማንደርደሪያ ነው
  - ቤት መምቻው ግን ፬ቱ ንባባት ፬፬ ነው።።

የዕዝል ክብር ይእቲ

- መጀመሪያ በዕዝል በግዕዝ ጉባኤ ቃና ነው ተቀባዩም ከማሁ
  - ሐረጉ ተነሽ ተጣይ ሰያፍ ከ፬ እስከ፭ ወዳቂ ከ፫ እስከ፭
  - ቤት መምቻውም ከማሁ
- ፪ኛው ቤትና ፫ኛው ቤትም ከማሁ
- ፬ኛውም እንደ መጀመሪያው ነው።።

የዕዝል ዕጣነ ሞገር

- መጀመሪያ ያለሐረግ በዕዝል በግዕዝ እስከ ቤት መምቻው ጉባኤ ቃና ነው
- የ፪ኛው ቤት መደቡ ከነተቀባዩ በዕዝልም በግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው
  - ቤት መምቻው ፬ቱ ንባባት ከ፬ እስከ፭ ነው እስከ፯ የሚሉም አሉ
- ፫ኛው ቤት እስከ ተቀባዩ ልውጥ ሚበዝኑ ነው
  - የቤት መምቻው መደቡ እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው
- የ፬ኛው ቤት መደቡ ከነተቀባዩ ልውጥ ሚበዝኑ ነው
- የ፭ኛው ቤት መደቡ እስከ ተቀባዩና እስከ ቤት መምቻው በዕዝልም በግዕዝም እንደ ጉባኤ ቃና ነው
  - ሐረጉ ወዳቂ ብቻ ፫፫ ነው
- ማንደርደሪያውም ከማሁ
- የአሥረ ንጉሡ መደቡ ከነተቀባዩ በዕዝል በግዕዝ እንደ ጉባኤ ቃና ነው
  - ሐረጉ ተነሽ ተጣይ ሰያፍ ከ፬ እስከ፭ ወዳቂ ከ፫ እስከ፭
  - ቤት መምቻው ከማሁ

- ፷ኛው ቤት እንደ ፭ኛው ቤት ነው
  - ሐረጉ ከማሁ
- ከ፱ኛው ቤት ይዞ እስከ ፲፭ኛ ው ቤት ከሥላሴ መጽፊያ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ያለው ነው አይለወጥም::

➢ ፴ ያላቸው ቅኔዎች

❖ ለሚበዝኑ ከመጨረሻው ቤት

❖ ለዋዜማ ከ፱ኛው ቤት

❖ ለመወድስ ከ፯ኛው ቤት ነው

✓ የዜማውም ልክ በግዕዝ ነው እንጅ በዕዝል አይደልም

✓ ከ፴ው ቀጥሎ ያለው መደብ ሁሉ በግዕዝ በግዕዝ ብቻ ይነሳል፡፡

➢ ነድ ያላቸው ቅኔዎች

❖ ለሥላሴ ከ፭ኛው ቤት

❖ ለዕዝል ዕጣነ ሞገር ከ፲ኛው ቤት ሲኾኑ

✓ ቀጥሎ ያለው መደብ በግዕዝ በግዕዝ ይነሳል ለቡ፡፡ ፣

የሕንጼሃ

- መደብ መጀመሪያ ወዳቂ በተለየ ከ፭ እስከ ፲
  - ዳግመኛም መደቡ እስከ ተቀባዩ በልውጥ ሚበዝኑ ይጀምራል
  - ቤት መምቻው ደግሞ በጉባኤ ቃና ቤት መምቻና በልውጥ ሚበዝኑ ነው
- ማንደርደሪያው እንደ ተለመደው ሲኾን ማስነሻ ቢኖረውም ባይኖረውም ይኾናል፡፡
  - የተለመደው ግን ያለ ማስነሻ ነው ባጭር ማንደርደሪያም ይኾናል::

የሐዋርያቲሁ ከበበ

- መደቡ እስከ ተቀባዩ እንደ ዕዝል ጉባኤ ቃና ሲኾን

❖ ተቀባዩ ያለሰያፍና ያለወዳቂ ተነሽ ተጣይ ብቻ ቤት እየመታ ነው

- ቀጥሎ ያለው መደቡ እስከ ተቀባዩ የጉባኤ ቃና ቤት መምቻ ነው
  - ሐረጉ ልውጥ ሚበዝኑና የዘይእዜ መደብ እስከ ማረፊያው ነው አይለወጥም
  - ✓ ኮኖሙ አበ ወእመ ያለው ወወላዲተ በል
- መጨረሻው ቤት እንደጉባኤ ቃና ቤት መምቻ ነው አስተውል ተፈጸመ::